የስር ፍ/ቤቶችም ይህን በሕግ የተመለከተውን የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ሥርዓት ባለመከተል ውሣኔ መስጠታቸው ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00676 መጋቢት 30 ቀን 1997 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38807 መጋቢት 22 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ተጠሪ መውሰድ ያለባት ድርሻዋ ማለትም የቤቱ እና የቤት እቃዎቹ ግማሽ ነው ብለናል፡፡ በዚህ መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈፀም ለስር ፍ/ቤቶች ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ



የሰ/መ/ቁ. 24625

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ሳድያ አሕመድ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ራሕማ ዓሊ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

አቤቱታው የንብረት ይገባኛል ጥያቄን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የወረዳ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተችው ተከሣሽ የሟች ባለቤቱ ማሩ ሱሌይማን ንብረት የሆነ ቤት ይዛ ስለምትገኝ የእኔንና ከሟች የወለድኩትን ልጄን ድርሻ ታካፍለን በማለት ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ከሣሽና ተከሣሽ የሟች ሚስቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም የቤቱን ግማሽ ሁለቱ ይካፈሉ፡፡ ግማሹን ደግሞ ለልጁ ይሁን በማለት ሲወስን፣ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛ ፍ/ቤት ግን ቤቱ የተገዛው ሟች እና ተጠሪ ባፈሩት ገንዘብ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት አመልካች ከቤቱ ልትካፈል አይገባም ሲል ወስኖአል፡፡ የመጨረሻውን ይግባኝ የሰማው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 2 ቀን 1998 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አከራካሪው ቤት አመልካችና ማሩ ሱሌይማን በጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ የተገዛ ሆኖ ሳለ፣ አመልካችና

ማሩ ሱሌይማን አብረው አልኖሩም፣ ቤቱ የተገዛበት ገንዘብም ማሩ ሱሌይማን ከተጠሪ ጋር በነበረበት ጊዜ የተገኘ ነው በሚል ምክንያት አመልካች ከቤቱ ድርሻ የላትም የመባሉን አግባብነት መርምሮ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንኑ ነጥብ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አከራካሪው ቤት የተሠራው በአመልካች እና በሟች ማሩ ሱሌይማን መካከል ተመሥርቶ የነበረው ጋብቻ ፀንቶ በነበረበት ወቅት ነው፡፡ በተጋቢዎቹ መካከል የተመሠረተው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ወቅት የተገኘ ንብረት የተጋቢዎች የጋራ ሃብት ነው ተብሎ የሕግ ግምት እንደሚወሰድበት በሕግ ተደንግጓል፡፡ ይህ የሕግ ግምት ቀሪ ማድረግ የሚቻለው አንደኛው ተጋቢ ንብረቱ የግል ሃብቱ እንደሆነ ካስረዳ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደሚታየው አከራካሪው ቤት የሟች የግል ንብረት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ቤቱ የሟች የግል ንብረት መሆኑ በሕግ አግባብ ካልተረጋገጠ እና ከፍ ሲል የተጠሰቀውን የሕግ ግምት ቀሪ የሚያደርግ የተለየ ሁኔታ እስከሌለ ድረስ አመልካች በቤቱ ላይ መብት የላትም ለማለት የሚቻልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር አመልካችን ከንብረቱ እንዳትካፈል ማድረግ ደግሞ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአማራ ብ/ክ/መ/የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07983 ታሕሣሥ 22 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05615 መጋቢት 7 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡



2. በአማራ ብ/ክ/መ/ የደባርቅ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቶአል፡፡ በመሆኑም የንብረቱ ክፍፍል በዚሁ ወረዳ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት ይፈጸም ብለናል፡፡

ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ